የሰ/መ/ቁ. 38228

ታህሣሥ 7 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሐጂ መሐመድ አወል ረጃ - ጠ/ደሣለኝ አለሙ ክብረት

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ዲኖ በሺር

2. ወ/ሮ ዘይቱ አረጋ

} ጠ/ አምሃ ነጋሽ ቀረቡ፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሁከትን ጉዳይ የሚመለከትን ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በሰበታ ወረዳ ካራብህርቡ ቀበሌ ገ/ማኀበር ውስጥ ሁለገብ የአረብኛ እና የሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል አቋቁው እየሠሩ ባለበት ወቅት ተጠሪዎች ድንበሩን ለመከላከል የተቆፈረው አፈር በመሙላት፣ የጥበቃውን ቤት በማፍረስና የተማሪዎቹን መኖሪያ በቁፋሮ በማናጋት ሁከት እየፈጠሩ በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ በሁከቱ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ሁከት ተፈጠረበት የተባለው ቦታ በአመልካች ይዞታ ስር መሆኑና በዚሁ ቦታ ላይ ተጠሪዎች ሁከት መፍጠራቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠ ሁከቱ እንዲወገድ፣ በሁከቱ ምክንያት ለደረሰው ተጠሪዎች ብር 4500.00 /አራት ሺህ አምስት መቶ/ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይዞታ የሚረጋገጠው በፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት ከሚመለከተው አስተዳደር መ/ቤት በተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም ካርታ ነው፣ አመልካች ይዞታው የራሣቸው መሆኑን ለማስረዳት ይህን መሰል የሰነድ ማስረጃ አላቀረቡም፣ ስለሆነም ባለይዞታ መሆናቸውን ሳያስረዱ ተጠሪዎች ሁከት ፈጥረዋል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጠረበት ነው በማለት ውሣኔውን ሽሯል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የሁከትን ጉዳይ ለመወሰን አመልካች በፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት ከአስተዳደር መ/ቤት የተሰጠ የባለይዞታነት ማረጋገጫ መቅረብ አለበት በማለት የሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ተጠሪዎችም ለቀረበው የሰበር አቤቱታ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በይዞታቸው ላይ ተጠሪዎች ሁከት እየፈጠሩ በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ በሁከቱ ምክንያት ለደሰረሰው ጉዳት ኪሣራውን ተጠሪዎች እንዲከፍሉ ነው፡፡ በይዞታው የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተነሣበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንዲመለስለት ወይም የተነሣው ሁከት እንዲወገድለት እንዲሁም ስለደረሰበት ጉዳት ኪሣራ እንዲሰጠው መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1149/1/ ሥር

ተመልክቷል፡፡ ይዞታ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 1140 ሥር ትርጓሜ ተሰጥቶታል፡፡ ይዞታ ማለት አንድ ሰው አንድን ነገር በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው ባለይዞታ ነው ለማለት በግድ በይዞታው ላይ ባለሃብት መሆን እንደሌለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት አንድን ነገር በእጁ አድርጎ በእውነት ያዝበት የነበረ መሆኑን ካስረዳ ባለይዞታ መሆኑ ይረጋገጣል ወደ ፍ/ሕ/ቁ. 1195 ስንመለስ ግን ይህ ድንጋጌ የሚገናረው ስለባለሃብትነት /ownership/ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው የማይንቀሣቀስ ንብርት ባለሀብት መሆኑ ከሚመለከተው አስተዳደር ክፍል የሚሰጠውን የባለሃብትነት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ማስረዳት ይችላል፡፡ በእርግጥ መሬት የማይንቀሳቀስ ንብረት ቢሆንም የመሬት ባለሀብት መሆን ባይችልም የመሬቱ የይዞታ ባለሀብት መሆኑን በማረጋገጥ ግን ተመሣሣይ ማስረጃ ማቅረብ ይገባል፡፡ በመሆኑም በፍ/ሕ/ቁ. 1140 እና 1195 መሃከል የሰፋ ልዩነት አለ፡፡ የመጀመሪያው አንድን ነገር ይዞ መገልገል ባለይዞታ የሚያደርግ መሆኑን የሚልጽ ሲሆን ሁለተኛው ግን አንድን ነገር ይዞ መገልገልን ብቻ ሣይሆን ከዛ ባለፈ የዚሁ ነገር ባለቤት መሆንን ለማረጋገጥ የሚያገለግል ድንጋጌው ነው፡፡ ስለሆነም የሁከትን ክስ ለማቅረብ ከሣሽ ማስረዳት ያለበት ሁከት ተፈጠረ የተባለበትን ነገር በእጁ አድርጎ በውነት ያዝበት የነበረ መሆኑን ብቻ እንጂ የዚሁ ነገር ባለሃብት መሆኑን አይደለም፡፡ ስለሆነም የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት አመልካች ባቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ክስ የፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት አድርጎ መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች ሁከት ተፈጠረ የተባለበትን በእጃቸው አድርገው ያዙበት የነበረ ለመሆኑ እና ተጠሪዎችም ሁከት የፈጠሩ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት ለማለት አይቻልም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58254 በ16/04/2000 የሰጠው ውሣኔ እና በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35850 በ12/07/2000 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19195 በ04/11/99 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች በአመልካች ቦታ ላይ የፈጠሩት ሁከት ሊወገድ ይገባል፡፡ በሁከቱ ምክንያት በደረሰው ጉዳትም ብር 4500.00 /አራት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ